# በስደት የኢትዮጲያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ

## Coordinating committee of exiled members of Ethiopian Teachers Association

### የተሰጠ መግለጫ

**ሐምሌ 19 ቀን 2004 ዓ.ም**

## ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም

**"ትውልድ ገዳይ የትምህርት ፖሊሲ" ብለን ስንጮህ ሰሚ አጣን! አሁንስ?!**

ባለፉት መግለጫዎቻችን ሰለ መምህርነት ሙያና ክብር፣ መምህራን ያላቸው ማህበራዊ ሥፍራ (Social Status) እና ሙያው የሰውን ልጅ ሙሉ ስብእና እንዲላበስ በትምህርት የመቅረጽ ሃላፊነት እንዳለበት፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሕዝብ ተከተታይ ትውልድ በመልካም ባህልና ሥነምግባር፤ ማህበራዊ ትስስሩ እንዲቀጥል የማድረግ ራዕይ ያነገበ መሆን እንደሚገባው አሳይተናል። የተማረ የሰው ሀይል በማፍራትም በሳይንስና ቴክኖሎጂ በመታገዝ አገሪቱ በብልጽግና ጎዳና እንድትራመድ መጣርና በተግባር ማሳየትም የሚጠበቅበት ስለመሆኑም በብዙ አጋጣሚዎች ቁምነገሮችን ለማስተላለፍ ሞክረናል።

በነዚህና በመሳሰሉት ጉዳዮች መነሻነት መምህራን በየጊዜው በተፈራረቁ የአገዛዝ ስራቶች ውስጥ ሕዝባዊ ጥያቄዎችን በማንሳት መራራ ትግል እያካሄዱ መስዋዕትነት መክፈል ዕጣ ፋንታቸው ከሆነ ቆይቷል። ይህ እንዳለ ሆኖ ለሙያና ለአገልግሎታቸው ተመጣጣኝ የሆነ ደመወዝ እንዲከፈላቸው፤ ለሙያቸው ማሻሻያ የተለያዩ የትምህርት ዕድሎች (ኮርሶች) እንዲመቻቹላቸውና በሚያካብቱት ዕውቀትና ልምድ አመርቂ ውጤት ለማስመዝገብ እንዲቻል ይጥራሉ። ከዚህ በተጓዳኝ አምርረው የሚታገሉለት የትምህርት ጥራት መጠበቅ እና ለሁሉም ዜጋ በሁሉም አካባቢ ያላድልዎ በእኩልነት መዳረስን መርህ አድርገው በጽናት እየታገሉ ቆይተዋል። ይህ በጎ አመለካከታቸውና ጥያቄያቸው ግን ቀደም ሲል በዘውዳዊው ሥርዓት፣ ቀጥሎ በወታደራዊው ደርግ አሁንም በወያኔው አምባገነን እና ዘረኛ ሥርዓት በቀና የሚታይ አልሆነም።

በተለይ ወያኔ/ኢህአዴግ ከጫካ በጠመንጃ ሀይል መጥቶ ራሱን መንግስት ብሎ ከሰየመ በሁዋላ ኢትዮጵያ የምትባል እንደአገር፣ ኢትዮጵያውያን የሚባሉ ዜጎች እንደ ሕዝብ የሚታወቁበትና በህልው የሚቀጥሉበት ሁኔታ እንዳይኖር እየሠራ በመሆኑ ለዕድገትና ብልጽግና ወሳኝ የሆነውን ትምህርትና በትምህርቱ ሥራ ወሳኝ የሆኑት መምህራን በቅድሚያ ተጠቂ ሆነዋል።

የአሠራሩ ብልሹነትና የጥፋቱ ሁሉ መንስኤም ከትምህርት ፖሊሲው ቀረጻ ይጀምራል። የትምህርት ፖሊሲውና መርህ-ግብሮቹ በይድረስ ይድረስ ከመውጣቱም በላይ ባለድርሻ አካላትን (Stake Holders)

ማለትም መምህራንን፣ ተማሪዎችን፣ ወላጆችንና አግባብ ያላቸው ሙያተኞችን ተሳትፎ ያላካተተ በውይይት ያልዳበረ በሕዝብም ተቀባይነት ያላገኘ ነበር። በወቅቱ የወያኔው ሥርዓት ቀዳሚ ትኩረት ሰጥቶ የተጠመደበት ጉዳይ ስለ ተተኪው ትውልድ መጻኤ ዕድልና የአገሪቱ የወደፊት ራዕይ ሳይሆን ለወቅታዊ የፖለቲካ ፍጆታውና ለሥልጣን መቆያ ስልቱ ነበር። በመሆኑም የሕዝቡን ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ ያላገናዘበ ከየባዕድ አገሩ ተቃርሞ በተደረተ የትምህርት ፖሊሲ አገሪቱን ቤተሙከራ አደረጋት።

ይህን አገር በቀል መሠረት የሌለውን ፖሊሲ ዓለም አቀፋዊ ይዘት ለማላበስ በመሻት የዓለም ባንክ (World Bank) የዓለም የገንዘብ ድርጅት (International Monetary Fund) ያቀረቡለትን ቅድመ-ሁኔታዎች ሳያንገራግር ተቀብሎ በመዋቅር ማስተካከያ (Structural Adjustment) ፕሮግራም የትምህርት፣ የጤና፣ የሠራተኛ ቅነሳ ዕቅድ እንዲያወጣ ታዞ ተግባራዊ አደረገ። ከዚያ በሁዋላ በአገሪቱ በሞላ በሁሉም መስክ የታየው ዝብርቅርቁ የወጣ የውድቀት አዙሪት ሆነ።

ወደተነሳንበት ነጥብ ወደ ትምህርቱ ሂደት ስንመለስ ወያኔ/ኢሕአዴግ ወደ መንግሥትነት ከመምጣቱ በፊት የትምህርቱ ዕርከን ከ1ኛ-6ኛ ክፍል የመጀመሪያ ደረጃ፣ 7ኛ-8ኛ መለስተኛ 2ኛ ደረጃ፣ ከ9ኛ-12ኛ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ በሚል ነበር የተዋቀረው። በአንፃራዊ መልኩ ሲታይ ይኸኛው ጥራት፣ ግብና ይዘት ነበረው። በተለይ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ለ4 ዓመታት የሚያቆየው አሠራር ተማሪዎች በዕድሜም በዕውቀትም ብስለት የሚያገኙበት በመሆኑ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ለዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች ጥሩ መጋቢ የመሆን አጋጣሚው የተሻለ ነበር።

የወያኔ መንግስት ይኸን ቀይሮ ከ1ኛ-4ኛ ክፍል የመጀመሪያ ሳይክል፣ ከ5ኛ-8ኛ ሁለተኛ ሳይክል፣ 9ኛ እና 10ኛ ክፍል 2ኛ ደረጃ፣ ቀጥሎ ያሉትን የመሰናዶ የሚል ስያሜ አውጥቶ ተንቀሳቀሰ። በሂደቱ የትምህርቱ ጥራት ሳይሆን ትኩረቱ በብዛት ላይ በማነጣጠሩ በከተማም በገጠርም በቅስቀሳና አንዳንድ ቦታም በግዴታ ጭምር ሕፃናት ወደ ት/ቤት እንዲጎርፉ ተደረገ። መምህራንም በተለይ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ በየመንደሩ እየዞሩ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ት/ቤት እንዲያመጡ እንዲያስገድዱ ግዴታ እንደተጣለባቸው ይታወሳል። በዚህ ምክንያት በአንድ የመማሪያ ክፍል የሚታጎሩት ሕፃናት ያለማጋነን እስከ 150 ይደርሱ እነደነበር ለሚመለከታቸው አካላት በሪፖርት ይገለጽ እንደነበር አሌ አይባልም። በመጀመሪያ ሳይክል ተማሪዎች ወደ ተከታዩ ክፍል የሚያልፉት በፈተና ሳይሆን በትምህርት አመት(Acadamic year) ቆይታቸው በመሆኑ 5ኛ ክፍል የሚገቡት ተማሪዎች ሌላው ቀርቶ ሆሄያትን በወጉ እንኳን ሳይለዩ የሚደርሱት ቁጥራቸው ቀላል አይደለም።

በሁለተኛው ዙር ማለትም ከ5ኛ-8ኛ ክፍል ያለውም በጥራት ላይ ያልተመሠረተ ሆኖ በተለይ 8ኛ ክፍል ላይ ብሔራዊ ፈተና ተፈትነው የሚወድቁት እየበዙ በገጠር ያሉት ወደ ግብርና እና ከብት ጥበቃ፣ በከተማ ያሉት ደግሞ

ለጎዳናለ ተዳዳሪንት ተዳርገዋል። ከሁሉም የባሰው የመሰናዶ ፕሮግራም በሚባለው ለመታቀፍ በትምህርት ውጤታቸው ተወዳዳሪ የሚሆኑት እጅግ ጥቂቶች ስለነበሩ በዚህ እርከንም የሚወድቁት ቁጥራቸው በርካታና በለጋ ዕድሜያቸው ከትምህርት ዓለም ተገልለው የወላጅና የአገር ሸክም እንዲሆኑ የተፈረደባቸው ሆነዋል። ከዚህ ወደላይ ባሉት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትም የተንፀባረቀው ብዙ ዩኒቨርሲቲዎችንና ኮሌጆችን ከፍቶ በ10 ሺህ የሚቆጠሩ ተማሪዎችን ማሳተፍና ማስመረቅ እንጂ የጥራቱ ነገር በዚህ ደረጃም ትኩረት የተሰጠው ሆኖ አልታየም። ለዚህ አባባል ማጠናከሪያ የሚሆን ከዘህ ቀጥሎ ለመጥቀስ እንወዳለን።

በተለያዩ የአገሪቱ ዩኒቨርሲቲዎች የሚያስተምሩ አብዛኛዎቹ የመጀመሪያ ዲግሪ ብቻ ያላቸው ሆነው፣ ሁለተኛ ዲግሪና ዶክትሬት ያላቸው እጅግ አናሳ በሆኑበት፤ ዩኒቨርሲቲዎችን የምርምር ተቋማት ለማድረግና በምህንድስና፣ በህክምና፣ በግብርና፣ .......... መስኮች ክህሎቱ ያላቸውን ዜጎች ማፍራትና በሙያቸው ለአገሪቱ የሚያበረክቱት አገልግሎት ይኖራል ብሎ እንዴት መጠበቅ ይቻላል?

ከአሁን በፊት በደረሰን መረጃ መሰረት ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ ከተለያዩ ዲፓርትሜንቶች ለመመረቅ የተዘጋጁ ተማሪዎች የመመረቂያ ጽሑፋቸውን በቡድን በቡድን እንዲያቀርቡ መደረጉ የትምህርት ጥራት ምን ያህል እየዘቀጠ መሔዱን ነው የሚያመለክተው። ለዚህ የተሰጠው ምክንያት የመመረቂያ ጽሑፉን ሊገመግሙ የሚችሉ ዕውቀቱም ያላቸው መምህራን እንደሌሉና ከተማሪዎቻቸው በተመሳሳይ የዕውቀት ደረጃ ላይ ሆነው የሚገመግሙበት አቅም የሌላቸው እንደሆነ ነው። ስለትምህርት መውደቅና ዋጋ ማጣት መናገርና ማሳወቅ የተገደድነው ዕውነታው የሚታይና ይህ የጥፋት ተግባር አንድ ቦታ መቆም እንዳለበት በማለም ነው። የጥፋቱ መገለጫዎች ዘርፈ ብዙ ናቸው። የትምህርቱ አስተዳደርና የአመራር ቦታዎች የሚያዙት ዕውቀትና ሙያ ባላቸው ሳይሆን ለገዢው ፓርቲ ታማኝና ሎሌዎች በሆኑ ግለሰቦች ነው። ይህም ከት/ቤት ርዕሰ መምህር ጀምሮ እስከ ከፍተኛው መዋቅር እርከን ድረስ ይደርሳል። ት/ቤቶች ምቹ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲፈጠርባቸው በአደረጃጀት በሰው ሀይል ምደባ፣ በመጻሕፍትና፣ በቤተ-ሙከራ አቅርቦት መሟላት ወሳኝ ሆነው ሳለ እነዚህ የተሟሉባቸው  የትምህርተ ተቋማት ቁጥር በጣት የሚቆጠሩ ናቸው።

ወያኔ/ኢህአዴግ ከማስመሰል በቀር ከልቡ ለህዝብ የሚሰራ አይደለም። የትምህርትን ጥራት አስጠብቃለሁ ብሎ ስድስት ፕሮግራሞች ያሉት ፓኬጅ አቅዶ በየት/ቤቶቹ ግድግዳና ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ የፕሮፓጋንዳ ስራ እንደሚሰራ ይታወቃል። መምህራንና አመራሩ እንዲያውቁት ከመሠልጠናቸው ባለፈ በተግባር እንዲታይ አላደረገም። ከዚሁ ጋር ተያይዞም በተለይ በአዲስ አበባ ደረጃ ፤መለያ ነጥብ ወጥተው ለጥናት ከተበተኑ በሁዋላ ደረጃቸውን የጠበቁ የተባሉ ት/ቤቶች ቁጥር እጅግ አናሳ እንደሆኑ ነው የታወቀው። በዚህም ለማሻሻያና ለእርምት

የተሠራ ነገር የለም። ሥርዓቱ የሚታወቀው በማስመሰል፣ በውሸትና በማጭበርበር ነው የምንለው ከዚህና ከመሳሰሉት ምግባሮቹ ነው።

የወያኔ መንግስት በ 2003 ዓ.ም የሥርዓተ ትምህርት ለውጥ አድርጌአለሁ በማለት ከመስከረም 4 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ የመምህራን ስብሰባ ማድረጉ ይታወቃል። የስብሰባውም ዋነኛ ዓላማ "የትምህርት ንቅናቄ" በሚል ጉዳይ የትምህርት ጥራትን ለማምጣት በሚል ሽፋን የአምስት ዓመቱን የዕድገትና የትራንሰፎርሜሽን ዕቅድ ነበር ሰበካ ያካሄደው። የትምህርት ጥራት ግን የአብዮታዊ ዲሞክራሲን ርዕዮት በማጥመቅ የሚመጣ አይደለም።

ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ለሁሉም የክፍል ደረጃዎች የሥርዓተ ትምህርት ለውጥ ተደርጓል በማለት ሥርዓተ ትምህርቱን ተከትሎ አጋዥ የትምህርት መጻሕፍት የታተሙ ሲሆን በተያዘው ዓመት (2003) በ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተግባራዊ እንደሚሆን ለዚህም 150 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር መመደቡን ት/ርት ሚኒስቴር መግለጹ ይታወቃል። እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ መጻሕፍትን በየትምህርት ዘመኑ መለዋወጥና ሥርዓተ ትምህርቱን ሙሉ ለሙሉ መቀየር የተለያዩ ነገሮች መሆናቸውን ነው። ወያኔ የሲለበስ ለውጥ (የሥርዓተ ትምህርት ቅደም ተከተል) ለውጥ በማድረግ ብቻ ሥርዓተ ትምህርቱ እንደተለወጠ አድርጎ በአደባባይ ደስኩሯል። የሥርዓተ ትምህርት ለውጥ ሳይደረግ የመረጃ መጻሐፍት ( Text ) ለውጥ በተደጋጋሚ ማድረግ እንደ መፍትሔ ተወስዷል። በአንድ የትምህርት ዘመን ዓመት እንኳን ሳያገለግሉ በሌላ መጻሕፍት መተካት፣ መጻሕፍቱ በመምህራን አስተያቶች ያልዳበሩ መሆን፣ በየጊዜው በሚታተሙት መጻሕፍቶች የባከነው ገንዘብ መጠነ ሰፊ መሆን፣ የታተሙት መጻሕፍት የክፍል ደረጃ የማይመጥኑና በግድፈት የተሞሉ መሆን፤ የመማር ማስተማር ሂደቱን ከንተቱት ውስጥ ዋነኞቹ ናቸው። ከዚህም ሌላ ለመምህሩ ቅድመ - ትውውቅ ያልተደረገለት በመሆኑ መምህሩ አድማጭ እንጂ ተሳታፊ አልነበረም። ለመሆኑ መምህራን የመማር ማስተማር ግዳጃቸውን እንዳይፈጽሙ እና ከምርምር ተግባር እንዲርቁ በተደረገበት ሁኔታ፣ በነፃነት የመሰብሰብ አካዳሚ መብታቸው በተገፈፈበት ሁኔታ፣ ወደ ሌላኛው እርከን መሸጋገር ያቃታቸው ተማሪዎች እንዲያልፉ መምህራን በትእዛዝ በሚገደዱበት ሁኔታ፣ ይባስ ብሎ ወያኔ የትምህርቱን ጉዳይ እንዳሻው በሚቀያይርበት ሁኔታ ዕውን የትምህርት ጥራት ይጠበቃልን? በአጠቃላይ በዚህ መልክ ከቶውኑም የትምህርት ጥራት ሊመጣ አይችልም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የአገሪቱ ጉዳይ እና ባጠቃላይ የተተኪው ትውልድ ጉዳይ ባለቤት በመሆኑ ጥራት ያለው የሕዝብ ትምህርት (Quality Public Education) በሁሉም መስክ ወሳኝነት ስለሚኖረው የትምህርቱን ሥራ ከውድቀት መታደግ የግድ ይለዋል። በዚህ ረገድ በመማር ማስተማሩ ሙያ የተሰማሩ መምህራን ከፍተኛ ሚና ስላላቸው የትምህርቱን ሥራ ማከናወን የሚችሉበት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው። በተለይም በሙያው ምልመላና

ሥልጠና፣ ምደባ እና ደመወዝ፣ ግምገማና እድገት፣ የአካዳሚ ነፃነት እና በነፃ የመደራጀት መብት ለትምህርቱ ዕድገት ቁልፍ እና ዋነኛ የማዕዘን ደንጋዮች ናቸው። በአሁኑ ጊዜ የሚታየው የወያኔ/ኢህአዴግ መንግሥት አካሄድ ግን ከዘህ በተቃራኒው ነው።

በአሁኑ ጊዜ መምህራን ያሉበትን ነባራዊ ሁኔታ ስንቃኝ ግን ነገሮች ከድጡ ወደ ማጡ ሆነውባቸዋል። ባለፈው መጋቢት ወር መምህራን ችግሩ ጸንቶባቸው ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸውን በመጠቀም የሥራ ማቆም አድማ በማድረግ መሠረታዊ እና ሕጋዊ ጥያቄያቸውን ለወያኔ መንግሥት አቅርበው ነበር። ይሁን እና ከተራ የኢህአዴግ ካድሬ እስከ ከፍተኛ ባለሥልጣናት፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጨምሮ ለጥያቄዎቻቸው የሰጡት መልስ አሳፋሪ እና የመምህሩን ሞራል የነካ፣ የሙያውን ክብር የተዳፈረ አጠቃላይ ሕዝቡንም ያሳዘነ ድርጊት ነበር። መምህራን ከሥራ ተባረዋል፣ ሙያ ማህበራቸው ከበፊቱ በበለጠ በወያኔ ትዕዛዝ ከት/ቤት መሠረታዊ መምህራን ማህበር እስከ አገር አቀፍ ያለው በካድሬ መምህራን እንዲያዝ ተደርጓል። የመምህራን ሕይወት በሽብር ተውጧል፣ በሽብርተኝነት በወያኔ ኢህአዴግ ተከሷል። እንደማንኛውም ሲቪል ሠራተኛ ማግኘት የሚገባቸው  የዓመት  ዕረፍት ፈቃድ ተነፍጓቸዋል። የክረምት የዕረፍት ጊዜያቸው የፖለቲካ ጥምቀት ማስኬጃነት ወያኔ በማስገደድ ይጠቀምበታል። የዘንድሮውን ለየት የሚያደርገው መምህራን የመብት ጥያቄ በማንሳት ሥራ እስከ ማቆም በመድረሳቸው፣ የእስልምና እና የኦርቶዶክስ ክርስትና ዕምነት ተከታዮች ባሳዩት የእምነት መብት የማስከበር ጥያቄ፤ እንዲሁም በጋምቤላና በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ሕዝባዊ ፀረ-ወያኔ እንቅስቃሴዎች በማየላቸው የተደናገጠው ወያኔ በት/ቤቶችም የተማሪዎች እንቅስቃሴና ተቃውሞ ይነሳል ብሎ በመስጋት  የዓመቱ ትምህርት ሊጠናቀቅ ከ1 ወር በላይ ሲቀረው ፈተና እንዲሰጥ እና ት/ቤቶች እንዲዘጉ አዞ ነበር። ነገር ግን በመምህራን፣ በተማሪዎችና በወላጆች በቀረበ ተቃውሞ ዕቅዱን ሊሰርዝ ተገዷል።

ይህ እንዳለ ሆኖ መምህራንን አባል ያልሆኑና አባል የሆኑ በማለት ለያይቶ በቅድሚያ ካድሬ መምህራንን ከሰኔ 25 እሰከ 28፣ በአማራ ክልል፣ ቀጥሎ ከሐምሌ 1 - ሐምሌ 5/2004 አዲስ አበባ በካድሬዎች አማካይነት እንዲሰበሰቡ ተደርጓል። ዓላማውም ለስድስቱ የትምህርት ፓኬጅ መርሐ-ግብር ተግባራዊ አለመሆን ተጠያቂው መምህሩ ነው ብሎ የወያኔን ግዙፍ ስህተትና ስውር ደባ በመምህራን ላይ ለማላከክ ነበር። መምህራን ግን አፈናውና እመቃው ቢጸናባቸውም የወያኔን ውንጀላ እና የተቃጣባቸውን መሠረተ ቢስ ክስ አልተቀበሉትም። እንዲያውም በአንዳንድ አካባቢ ስብሰባውን እየረገጡ የወጡ እነደነበሩ ታውቋል። አባልና ካድሬዎችን ለብቻ መሰብሰብ የፈለገውም በጋራ ስብሰባ ሲቀመጡ የራሱን አጀንዳ የሚያንፀባርቁ ሐሳቦች እንዲያነሱና ከብዙሃን መምህራን እንደቀረበ ለማስመሰል ነው። ባጠቃላይ ት/ቤቶች ሲከፈቱም ሆነ ሲዘጉ በስብሰባ የሚጠፋው ጊዜ የትምህርቱን ወቅት በእጅጉ ተሻምቶታል።

በመሠረተ ሀሳብ ደረጃ ስብሰባ እና ውይይት አስፈላጊ ቢሆንም ወያኔ ግን ለትምህርቱ ሥራና ለአገር ዕድገት የሚገደው ባለመሆኑ የስብሰባውን ቅኝት ለፖለቲካው ዓላማ ትርፍ ሲያውለው ይስተዋላል። ትምህርት በዘፈቀደ የሚከናወን ተግባር ሳይሆን  የዓመት፣ የንፍቀ-ዓመት የሣምንት እና የዕለት ተብሎ ዕቅድ ወጥቶለት ሳይዛባ የሚጠናቀቅ መሆን ነው የሚገባው። ወያኔ ግን ለፖለቲካ ሥራ ቅድሚያ በመስጠት የትምህርት ጊዜ እያባከነ ይገኛል።

እነዚህና የመሳሰሉት የወያኔ የመደናበር አሠራር መምህራንን በእጅጉ አማሯቸዋል፣ የሙያውንም ክብር ቁልቁል አውርዶታል። ስለሙያው መውደቅ ከሚዲያና ከተለያዩ ምንጮች ያገኘናቸውን እስኪ ለአብነት እንጥቀስ። ጁላይ 16/2012 በጀርመን የዶቼ በሌ የአማርኛው ሥርጭት ቢጋዜጠኛ ለቃለ-ምልልስ የቀረበችው ራህማ ናስር የተባለች የዲላ ከተማ ነዋሪና የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪ የሆነችው ሰለመምህራን ያየሁትን ልመስክር በማለት ትጀምራለች። እናቷም አባቷም መምህራን መሆናቸውን ተናገረች። ነገሩ ዕውነትነት ያለው ቢሆንም መምህራን የዕውቀት አባት ናቸው ብላ መናገር እነደሚከብዳት በምክንያት አስረዳች። በአሁኑ ጊዜ መምህራን በማህበራዊ ኑሮ ለሞት፣ ለሠርግ፣ ለክርስትና ለልደት ለመሳሰሉት ለመሳተፍ ገንዘብ ስለሚያጥራቸው ራሳቸውን እንዳገለሉ ገለጸች። ጋዜጠኛዋ በመገረምና በማዘን እንዴት ይኸን ያህል ከሌላው ሠራተኛ ክፍል የተጎዱ እነደሆኑ ጥያቄዋን አስከተለች። ራህማም በአሳማኝ ማስረጃ ስታቀርብ አንድ የሁለተኛ ደረጃ መምህር ደመወዙ ብር 1600 ቢሆን ጤፍ ብቻ ብር 1600 ተገዝቶ ሌላው ወጪ ሁሉ በምን ይሸፈናል? በሚል መልሷን አጠናክረዋለች ። የሚያሳዝነው የመምህራን ልጆች በወላጆቻቸው የኑሮ ሁኔታ የሚያዝኑ እንደሆነና ወደ መምህርነት ሙያም ለመግባት በጭራሽ እንደማይፈልጉ ያነሳችው ነጥብ ነው። እሷም መምህር ለመሆን እነደማትፈልግና ሥነልቦናዋ መነካቱን መናገር አልሸሸገችም። ከዚሁ ጋር በተያያዘም መምህራን በአስተዳደር ከሚደርስባቸው በደል በተጨማሪ የወር ገቢያቸው ከ15 ቀናት በላይ ሊያቆያቸው ባለመቻሉ ከሙያው የሚፈልሱት ቁጥራቸው እያሻቀበ ይገኛል። በአገር ውስጥ የተሻለ ክፍያ በመፈለግ ወደ ሌላ የሥራ መስክ የሚፈልሱት እነዳለ ሆኖ ወደ መካከለኛ ምሥራቅ እና ወደ አረብ አገሮችም መጉረፍ ጀምረዋል። ባለን መረጃ መሠረት ከሰሜን ወሎ ራያና ቆቦ በአንድ ሰሚስቴር ብቻ 147 መምህራን ወደ ተጠቀሱት አገሮች ተሰደዋል። ልብ በሉ አረብ አገር በግብርና በረሃ ለማልማት፣ ለፍየል እረኝነት፣ ሴቶች እህቶቻችን ደግሞ ለግርድና መዳረጋቸው የሥርዓቱን አስከፊነት ከማረጋገጡም በላይ በትምህርቱ ሥራና በሙያው ላይ ጣምራ ጦርነት ከፍቶ ትውልድን የመግደል እርምጃ እየተወሰደ ነው።

ቅን ልቦና ላለው ዜጋ የኮሌጅ ወይም የዩኒቨርሲቲ ምሩቅ ሆኖ "ኮብል ስቶን" አምራች፣ መንገድ ላይ ሻይና ዳቦ ቸርቻሪ፣ የታክሲ ተራ አስከባሪ፣ በጥንታዊ አስተራረስ ዘዴ በሬዎች ጠምዶ የሚያርስ ገበሬ ሆኖ ቢያይ ከልብ

እንደሚያዝን መጠራጠር አይቻልም። መቸም ይሉኝታም ሐፍረትም በተፈጥሮአቸው ቅንጣት ያህል የሌላቸው ወያኔዎች ይኸውም ፀጋ ነው፣ ምን አነሳችሁ በሚል መታበይ ይመስላል በሚዲያ ሳይቀር በጎ እንዳደረጉ መስለው ነጋ ጠባ ሊያደነቁሩን ይጥራሉ። በ10 ሺህ የሚቆጠሩ የዩኒቨርሲቲና የኮሌጅ ተማሪዎችን እያስመረቁ በተመረቁበት ሙያ የሥራ ዕድል እንዲያገኙ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ፋንታ ከላይ በተጠቀሱት ከፍተኛ የትምህርት ችሎታ በማያስፈልጋቸው ሙያዎች እንዲሳተፉ የሚያሳስብ ንግግር ከወያኔ ባለሥልጣናት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና በሌሎችም ኮሌጆች የምረቃ ወቅት ተደምጧል። ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም ለማለት ያነሳሳን ይህን የመሳሰሉና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ፀረ-ሕዝቡ ወያኔ የፈፀማቸው ድርጊቶች ፈጠው ስለወጡ ነው። የትምህርት ፖሊሲውም "ትውልድ ገዳይ ነው" እያልን መጮህችን ያለ ምክንያት አልነበረም፤ ይኸው የ አደጋው ዳመና ከመጥቆር አልፎ ዶፍ ሆኖ እየወረደ አገሪቱን እያጠፋ ነው።

በስደት የመምህራን ማህበር አስተባባሪ ኮሚቴ ለዚህ ሁሉ ችግር መንስኤ የወያኔ/ኢህአዴግ ዘረዘኛ ሥርዓት ስለሆነ መፍትሔው ይህን ፀረ-ሕዝብ ሥርዓት ማሰወገድና በምትኩ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን መታገል እንዳለብን ያሳስባል። በዚህ በኩል የሁሉም ህብረተሰብ ክፍል በትግሉ ላይ መሳተፍና ለአገር የሚከፈል መሥዋዕትነትም ከእያንዳንዱ የሚጠበቅ በመሆኑ መምህራንም ራሳቸውን በማደራጀትና የሙያ ማህበራቸውንም ህልውና በመጠበቅ ረገድ በስልት መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል። በተለይም በአሁኑ ወቅት በአገራችን የተለያዩ አካባቢዎች እየተቀጣጠለ ባልው የሕዝብ ትግል ውስጥ በመሳተፍ አገር አቀፍ መልክ ይዞ እንዲቀጥልና ይህን የሁሉ ችግሮች ምንጭ የሆነውን የወያኔ ዘረኛ ሥርዓት ለማስወገድ በጋራ መረባረብና በቆራጥነት መታገል ይጠበቅብናል።

ትምህርት ያለ ጥራት ዋጋ ቢስ ነው!

ኢመማ በትግላችን ይጠነክራል!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!

ለበለጠ መረጃ በ eta1941@yahoo.com በመጻፍ ሊገናኙን ይችላሉ